በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 250350
ታህሳስ 25 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጂባ ኑሪ- ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.ወ/ሮ ስርሰንጌ ባዴቦ - አልቀረቡም

2.አቶ ሽኩሬ ሳሊያ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ05/11/2015 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 23181 በቀን 29/10/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.20970 በ16/06/2015 ዓም የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ጣልቃ ገብ የነበሩ ሲሆን 1ኛ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ ከሳሽ፤2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ፍቺን ተከትሎ በተሰጠ የንብረት ክፍፍል ጉዳይ መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔውን ተከትሎ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር አዋሳኛቸው በክሱ ላይ የተመለከቱትን ሁለት መሬቶች ፤በመሬቱ ላይ ከሚገኙ ዛፎች፤ትልቅ የሳር ክዳን ቤት ጋር፤መልክና ግምታቸው በክሱ ላይ የተመለከቱትን የቤት እንስሳት፤ከእርሻው መሬት የተሰበሰበውን ምርት በትዳሩ ወቅት በጋራ ያፈሩ መሆኑን ገልፀው እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡2ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስም በንብረት ዝርዝሩ መጀመሪያ ላይ የተመለከተውን መሬት በቤተሰብ ጉባኤ ሶስት ቦታ ማለትም ለተጠሪዎችና ለአመልካች የተካፈለ በመሆኑ፤ሁለተኛውን መሬትም አመልካችን ሳገባት ለኒካ የሰጠኋት በመሆኑ፤ተንቀሳቃሽ ንብረቶቹንም አመልካች ያፈራቻቸው በመሆናቸው፤ከእርሻው የተሰበሰበውን እህልም አመልካች የእርሻ መሬቷን በመጠቀም ያፈራቸው በመሆኑ የክፍፍል ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም ጣልቃ ለመግባት አመልክተው ተፈቅዶላቸው ባቀረቡት ክርክርም በ1ኛ ተጠሪ በንብረት ዝርዝሩ መጀመሪያ ላይ ጠቅሰው ያቀረቡት የእርሻ መሬት በቤተሰብ ጉባኤ ለሶሰት ተካፍለን ለኔ በደረሰኝ ድርሻ ላይ ባህር ዛፍ ግራር ዛፍ አፍርቼ ና የሳር ክዳን ጎጆ ቤት በመስራቴ በይዞታው ላይ የሚገኙ ሆኖ እያለ ከዚህ በተጨማሪ የተጠቀሰው የእርሻ መሬትም 1 ጥማድ ከግማሽ ሆኖ በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሃከል ኒካ ሲታሰር በኒካህ የተሰጠኝ በመሆኑ የቤት እንስሳቱም ከወላጅ አባቴ ተሰጥተውኝ የተራቡ በመሆናቸው፤የስንዴ፤ማሽላና በቆሎ ምርቱም በድርሻ የእርሻ መሬቴ ላይ ያመረትኩት በመሆኑ በዚህ ድርሻዬ ላይ የክፍፍል ጥያቄ መቅረቡ አግባብ አይደለም፤ስለሆነም ድርሻዬ ተለይቶ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ፤በስፍራው በመገኘት ምልከታ አድርጎና ለጉዳዩ ገለልተኛ ናቸው ያላቸውን ምስክሮች ሰምቶ በሰጠው ውሳኔም ለጉዳዩ ገለልተኛ ናቸው በማለት የጠቀሳቸው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድ ላም ከነጥጃዋ፤ወይፈንና ጊደር የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ቢሆኑም እንስሳቱ የተራቡት የአመልካችም አስተዋፅኦ ታክሎበት በመሆኑ አመልካችና ተጠሪዎች እኩል ለሶስት እንዲካፈሉ፤የእርሻ መሬቶቹን በተመለከተ በተጠሪዎች ስም ተመዝግበው የነበረ መሆኑን፤ በቤተሰብ ጉባኤ ተከፋፍሏል የተባለውን መሬት አስመልክቶም ሳይከፋፋል ተጠሪዎች ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያስረዱ መሆኑን በመጥቀስ፤ግራ ቀኙ የሚኖሩባቸውን ሁለቱንም የሳር ቤቶች 2ኛ ተጠሪ መስራታቸው መረጋገጡን በማመልከት በቆሎ ማሽላና ስንዴው 1ኛ ተጠሪ በሚጠቀሙበት የእርሻ መሬት ላይ የተመረተ ቢሆንም እነዚህ የእርሻ መሬቶች ያልተከፋፈሉ የጋራ ሀብቶች በመሆናቸው 8 ጥማዱን መሬት ተጠሪዎች እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ ግማሽ አመልካች

እንዲካፈሉ፤የጫት ተክል፤ ባህር ዛፍ እና የሳር ክዳን ቤቱን በተመለከተ በ2ኛ ተጠሪና አመልካች ጥረት የተፈራ ንብረትን የያዘ በመሆኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ 1ኛ ተጠሪ ሊካፈሉ ይገባል፤3 ጥማድ የእርሻ መሬትን በተመለከተ ተጠሪዎች እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ ግማሽ አመልካች እንዲካፈሉ እንዲሁም የቤት እንስሳትን ግራ ቀኙ እኩል ሶስት ቦታ እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ከእርሻ መሬት ጋር በተያያዘ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን የቤት እንስሳትን በተመለከተ ግን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል አንድ ላም ከነጥጃዋ፤አንድ በሬና አንድ ጊደር በአመልካች አስተዋፅኦ የተራቡ በመሆናቸው ግማሹ ድርሻ የአመልካች ነው ቀሪውን ግማሽ ድርሻ ተጠሪዎች እኩል ሊካፈሉት ይገባል በማለት በዚህ ረገድ (ከቤት እንስሳት ጋር በተያያዘ ብቻ) የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔም ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪዎች የገጠር እርሻ መሬቶቹን አስቀድመው በመያዝ ሳር ቤትም ሰርተው እየኖሩበት እና ሲጠቀሙ ቆይተው አመልካች ሁለተኛ ሚስት ሆነው ሲገቡ ሌላ ሳር ቤት የተሰራላቸው መሆኑን፤1ኛ ተጠሪ የሚኖሩበት የሳር ቤት አርጅቶ ቢፈርስም 1ኛ ተጠሪና አመልካች በየራሳቸው የሳር ቤት ጀርባ እያለሙ ሲኖሩ የነበረ መሆኑን ማስረጃዎቹ እያሳዩ የስር የወረዳው ፍርድ ቤት ለአፈፃፀም በማያመች አኳኋን ፍርድ መስጠቱን በመተቸት እነዚህን መሬቶች አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር 8 ጥማድ መሬቱን አስመልክቶ ይዞታውን ከፊት ለፊት ከስፋቱ መጠን አጋማሽ ላይ በመነሳት በቁመት ለሁለት እኩል በመክፈል ከፊት ለፊት ጀምሮ ወደግርጌ ድንበር በማቆምና በመለየት አሀን ካለው የሳር ክዳን ቤት ከፊትና ከኋላ የሚገኝ ይዞታና ንብረት ለአመልካችና ለ2ኛ ተጠሪ የጋራ ድርሻ እንዲሆን፤ቀደም ሲል የ1ኛ ተጠሪ የሳር ክዳን ቤት የነበረበትን ቦታ ከፊትና ከኋላ ቋሚ ንብረትና ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ ነው ፤ሶስት ጥማድ የእርሻ መሬትን አስመልክቶ ግማሹ ድርሻ የ1ኛ ተጠሪ ቀሪው የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ድርሻ ነው በማለት የወሰነ ሲሆን የቤት እንስሳቱን በተመለከተ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም 1ኛ ተጠሪ ሳትቃወመኝ ከ2ኛ ተጠሪ ከተጋባሁበት የዛሬ 26 ዓመት ጀምሮ በይዞታው ላይ መጀመሪያ የነበረው የሳር ክዳን ጎጆ ቤት ፈርሶ ለ2ኛ ጊዜ የሳር ክዳን ጎጆ ቤት ሰርቼ ከ6 ልጆቼ ጋር እየኖርኩበት የምገኝ ሲሆን በዚህ ቤት ግንባታ ላይ 1ኛ ተጠሪ ምንም አይነት አስተዋፅኦ ባላደረገችበት ቤቱም በጋራ ለመኖር ታስቦ የሚሰራ ባልሆነበት፤በይዞታው ላይ ስኖር ቡና፤ጫትና ባህር ዛፍ ተክዬ ያለማሁትንና በየአመቱ እህል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እየዘራሁኝ ስጠቀምበት የምገኘውን ሁለት ይዞታዎች  የጋራ ንብረቶች ናቸው ተብሎ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የአመልካች የግል ንብረቶች ናቸው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ሁለቱም ሚስቶች የየራሳቸው ቤት ያላቸው ሆኖ እያለ አንዱ ከሌላዋ ትካፈል የተባለበትን እና 3 ጥማድ መሬት ለአመልካች በኒካ የተሰጣት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ 25% ከ2ኛ ተጠሪ ትካፈል የተባለበትን አግባብ በተመለከተ  በሰበር ሰሚው ችሎት ሊጣራ ይገባል ብሎ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ መርቷል፡፡ ይህ ችሎትም የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአንድ በኩል በሰ/መ/ቁ.22046 በሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በስልጣን ምክንያት ከሻረ በኋላ በሰ/መ/ቁ.23181 በሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ያፀናበትን አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

በዚህ አግባብም 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተመራበት አግባብ ምንም አይነት የስነስርዓት ግድፈት የሌለበትና የተፈፀመ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.22046 ግንቦት 10 ቀን 2015 ዓም በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ.20970 የሰጠውን ውሳኔ በስልጣን ጉዳይ መሻሩ በአግባቡ ነው፤የሳር ቤቱን አስመልክቶም ሁሉንም ንብረቶች ከጅምሩ ጀምሮ ያፈራነው ተጠሪዎች ስንሆን ተጠሪዎች ጋብቻችንን ከመሰረትን 35 አመት በኋላ የልጅ ልጅ ካየን በኋላ በ2002 ዓም እኔ በሰራሁትና ባፈራሁት ይዞታና ንብረት ላይ 2ኛ ተጠሪ አመልካችን ያገባት ሲሆን እኔ እኖርበት የነበረውን ቤት አርጅቶ ሲፈርስ 2ኛ ተጠሪ ሊሰራልኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጎረቤት ተጠግቼ እየኖርኩ የምገኝ በመሆኑ፤የስር ፍርድ ቤቶች ቦታው ድረስ በመሄድ አጣርተው የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የቤተሰብ ህጉን ፤የሰበር ውሳኔዎችንና የፌደሬሽን ምክር ቤት የህግ ትርጉሞችን መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስም ከአመልካች ጋር በተጋባንበት ወቅት በክፍፍሉ ጊዜ ለ1ኛ ተጠሪ ለብቻዋ ተለይቶ ተሰጥቷት ሶስታችንም የየራሳችን ይዞታ የነበረን ሲሆን የስር የወረዳው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከዚህ ጥሬ ሀቅ በተለየ ሁኔታ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች በጠየቀችው መሰረት ቢወሰንላት አልቃወምም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካችም በቀን 15/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡በግራ ቀኙ መሃል ያለው በሁለት የገጠር የእርሻ መሬቶችና በእነዚህ መሬቶች ላይ የተፈሩትን ተክሎች እና በአንደኛው የእርሻ መሬት ላይ የተሰራውን የሣር ቤት የሚመለከተው የሰበር ክርክር በተጠሪዎች መሀከል የነበረ ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የንብረት ክፍፍል ውሳኔን መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን የክልሉን የቤተሰብ ህግ መሰረት ያደረገ የሰበር ክርክር መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ክርክሮች እና ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጓቸው ክርክሮች ያሳያሉ፡፡እነዚህን ክርክር የቀረበባቸውን ንብረቶች በተመለከተም የዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ 8 ጥማዱን መሬት ተጠሪዎች እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ ግማሽ አመልካች እንዲካፈሉ፤የጫት ተክል፣ ባህር ዛፍ እና የሳር ክዳን ቤቱን በተመለከተ በ2ኛ ተጠሪና አመልካች ጥረት የተፈራ ንብረትን የያዘ በመሆኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ 1ኛ ተጠሪ ሊካፈሉ ይገባል፤3 ጥማድ የእርሻ መሬትን በተመለከተ ተጠሪዎች እኩል ከተካፈሉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ ግማሽ አመልካች እንዲካፈሉ ከወሰነ በኋላ ይህ የውሳኔ ክፍል በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመፅናቱ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀፅ 5(2) በተዘረጋው የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓት መሰረት አመልካች በተሰጡት ውሳኔዎች ቅሬታ ካላቸው ሊያቀርቡ የሚገባው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊሆን ሲገባ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካች ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰኑና ይህንን በይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ከክርክር አመራር አንፃር የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርም ሲገባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰሚ ችሎት በስር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 23181 በቀን 29/10/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.20970 በ16/06/2015 ዓም የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2.ይህ ውሳኔ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት እና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉ ከሆነ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡

3.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

## የልዩነት ሀሳብ

ስም በተራ ቁጥር 5 ላይ የተሰየምኩት ዳኛ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቤተሰብ ክርክር ሁለተኛ ይግባኝ የሌለ በመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም በሚል የተደረሰበትን መደምደሚያ የምስማማበት ነው። ነገር ግን አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሥረ-ነገሩ አቤቱታ ያቀረቡ በመሆኑና በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥረ-ነገሩ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት ሁለተኛ የሰበር አቤተታ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው አቤቱታቸው ከሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አንጻር ሊመረመር ሲገባ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ አዲስ ሰበር አቤቱታ እንዲያቀርቡ በአብላጫ ሃሳብ መታዘዙ ምክንያት የልዩነት ሃሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ።

አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው። ሁለተኛ ይግባኝ ከተወሰነ በኋላ ለሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበ በመሆኑ የሰበር ማቅረቢያ ጊዜ መቆጠር ያለበት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 323/2 መሰረት ቅሬታ የሚቀርብበት ውሳኔ ከተፈረደበት ቀን ጀምሮ ነው። በተያዘው ጉዳይ የሰበር ቅሬታው ጊዜውን ጠብቆ የቀረበ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የሰበር ቅሬታው የማቅረቢያ ጊዜውን ጠብቆ የቀረበ ነው ከተባለ በዚሁ መዝገብ የአመልካች የሰበር ቅሬታ ሊመረመር ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ስመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ጉዳዩን በሁለተኛ ይግባኝ የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑ የምስማማበት ነው፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለው በውሳኔ ከተገለጸ በኋላ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሥረ-ነገሩ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠው በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መነሻ ዋናው ጉዳይ ተመርምሮ

ውሳኔ እንዲሰጥ ሊመለስ ይገባ ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም የፍትሐ ብሔር ስነ-ስርአት ህጉ ዋና አላማ ክርክሮችን ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ ተከራካሪዎች ሳይጉላሉ ክርክራቸው እልባት እንዲያገኝ ማስቻል ነው፡፡ አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ የሰበር ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉ በመፍቀድ ዋናውን ጉዳይ እንዲመረመር አለማድረግ ተከራካሪዎችን ለጊዜ እና ወጪ ብክነት የሚዳርግና የፍትሐ ብሔር ስነ-ስርአት ሕጉ አላማ ጋር የማይሄድ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ከሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ አንጻር የግራ ቀኙን ክርክር በሥረ-ነገሩ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ሊመለስለት ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !